የሰ/መ/ቁ 36979

ሐምሌ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-**ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ግርማ ኃ/መስቀል ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሚስተር ሽሬሃሪ ብራማቫሪ ጉፓል - ጠበቃ አቶ ሀይልዬ ሣህለ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57672 የካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ(የአሁን አመልካች) አላግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ (ተጠሪ) የድርጅቱ ክፍለሀጉራዊ ሥራ አስኪያጅ በመሆናቸው የሥራ መሪ ናቸው፤ ጉዳያቸው በአሠሪና ሠራተኛ ችሎት መታየት የለበትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የያዘውን የሥራ መደብ ስያሜ በመመልከት ብቻ የሥራ መሪ ነው ማለት ስለማይቻ ስልጣን የለኝም ያልከው አላግባብ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት አከራክረህ ወሰን በማለት ጉዳዩን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመሠረቱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማከራከር ስልጣን የለኝም በማለት ያዘጋው በአግባቡ ነው፡፡ ከተጠሪ ጋር የተደረገው የሥራ ውል እና ከኢትዮጵያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአመልካች ተጠያቂነት ለተጠሪ የተሰጣቸው የሥራ ፈቃድ ማስረጃ ተጠሪ ሪጅናል ማኔጀር እንደሆኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ይህንን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 መሠረት አስቀርቦ እንዲመለከትልን ጠይቀናል፡፡ ፍርድ ቤቱ የጠየቅነውን ማስረጃ አስቀርቦ ሣይመለከት ተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ጉዳያቸው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ይታያል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የሚገባ ስለመሆኑ በውሉ አንቀፅ 7 እና አንቀጽ 12 የተመለከቱትን ሀይለ ቃሎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች የተጠሪን የሥራ ዝርዝርና የድርጅቱን መዋቅር በማቅረብ ተጠሪ ሥራ መሪ መሆናቸውን አላስረዳም፡፡ ይህ ከሆነ

“ክፍለህጉራዊ ሥራ አስኪያጅ” የሚለውን ስያሜ በማየት ብቻ ሥራ መሪ ናቸው ሊባል ስለማይገባ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ስለዚህ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጠተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በፅሑፍ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪው የሥራ መሪ መሆኑን በመግለፅ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በሌላ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡ አመልካች ተጠሪን እንድቀጥር የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ያቀረብኩት አቤቱታ መነሻ ለተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የተሰጣቸው የሥራ ፈቃድ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 መሠረት ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ እንዳይላቸው ጠይቀው ፍርድ ቤቱ ይህንን ማስረጃ ሣያስቀርብ ተጠሪ የሥራ መሪ አይደሉም በማለት ውሣኔ እንደሰጠባቸው በመግለፅ በሰበር ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ መሆናቸውን የሥራ ፈቃድም ያገኙት በዚሁ የሥራ ሀላፊነት ለመሠማራት መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት እንዲቀርብ የጠየቁት ማስረጃ የሥር ፍርድ ቤት ያላስቀረበው በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 345 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) መሠረት ማስረጃውን በማስቀረብ ውሣኔ መስጠት ነበረበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብላቸው የጠየቁት ማስረጃ ሣያስቀርብ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ የሚተላለፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ማስረጃ በማስቀረብና ጉዳዩን በማጣራት ውሣኔ ይስጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ